# ኢትዮጵያ «ዋካንዳ» ትሆናለች፤ ፍሬደሪክ ኩ፡

በስንታየሁ ግርማ sintayehugirma76@gmail.com

08-09-18

- ፍሬደሪክ በጣም በቅርቡ በቻይና የተመረተ የሚለው በኢትዮጵያ የተመረተ በሚለው ይተካል ይላል፡፡
- ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች በተለየ መልኩ ኢትዮጵያ ማንነት የተመሰረተው በቅኝ ገዢዎች ሳይሆን በኦርጋኒክ/ ተፈጥሮ የተገነባ ነው ያላል ፍሬደሪክ ኩ፡፡
- በባህል ሀብት፣ በታሪክ ኩራት እና ተለየ ማንነት ኢትዮጵያ አሁንም እንዳስጠበቀች ነው፡፡

ዋካንዳ በሆሊውድ የተሰራ ፊልም ሲሆን 1.2 ቢሊዮን ዶላር በማስገባት ሪከርድ አስመዝግቧል፡፡ ፊልሙ በቴክኖሎጂ የበለጸገች ግን የጥንቷን እና የበለጸገች አፍሪካን ባህል ያልረሳች አገር በፈጠራ ያሳያል፡፡ ይህቺ አገር በምስራቅ አፍሪካ የምትገኝ ናት፡፡ በብልጽግናው፣ በፈጠራው፣ በተማረ የሰው ሃይል ተወዳዳሪ የሌላት ግን ደግሞ በተናጠል የምትኖር አገር ናት፡፡ ፊልሙ በማህበራዊ ሚዲያ መነጋገሪያ ሆኗል፡፡ ይቺ አገር ኢትዮጵያ ናት ይላል ፍሬደሪክ ኩ፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ አፍሪካ ወደር የሌለው እድገት እያስመዘገበች ነው፡፡ አንዳንዶች አፍሪካ በህዳሴ ላይ ናት እያሉ ነው፡፡ ታላቅ ታሪክ ያላት እና በታሪኳ የምትኮራው ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የሆነ ኢንዱስትሪያላይዜሽን እየተገበረች ነው፡፡ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እና ለከተሞች መስፋፋት መሰረት እየጣለች ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የወደፊት ዋካንዳ ትሆን ይሆን?

ጸሀፊው እንደሚሉት እ.ኤ.አ ከ2004 እስከ 2014 በአማካይ በየአመቱ የ8 በመቶ እድገት አስመዝግባለች፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ከ11 በመቶ እያደገ የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል፡፡ ብዙዎች አፍሪካ አገሮች እድገት ሸቀጦችን ኤክስፖርት በማድረግ እና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የቻይናን መንገስት መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመከተል እድገት እያስመዘገበች ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት የእድገት ሞተር ሲሆን አገሪቱ አፍሪካ የማኑፋክቸሪንግ ማዕከል እየሆነች ነው፡፡ ይህ ስራ የተጀመረው በቀድሞው ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ነው፡፡ የምስራቅ ኤስያን እድገት ወደ ኢትዮጵያ በማምጣታቸው አድናቆት ይሰጣቸዋል፡፡ በመሰረተ ልማት ግንባታ መንግስት ጥሩ የመሪነት ሚና በመስራቱ እና የኢንዱስትሪ ዞኖች በመገንባቱ በአንድ ወቅት የጦርነት እና የረሀብ ምሳሌ የነበረችው አገር የፈጣን እድገት አገር እየሆነች ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሀገራትና የቀላል ኢንዱስትሪዎችን ማለትም በማኑፋክቸሪንግ በኮንስትራክሽንና በግብርና ላይ በማተኮር የኤስያን እድገት እየደገመችው ነው፡፡ በሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ እንኳ ከ11 አገራት 18 ኩባንያዎች በ140 ሄክታር

ኢንቨስት እያደረጉ ነው፡፡ ፓርኩ በሙሉ አቅም ወደ ስራ ሲገባ ወደ 60ሺህ ሰዎች የስራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ እተጠበቀ ነው፡፡



መንግስት መሰረተ ልማት ለመገንባት ቁርጠኛ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ1997 የነበረው 26ሺህ550 ኪ.ሜ መንገድ እ.ኤ.አ በ2011 ወደ 53ሺህ 997 አድጓል፡፡ ታላቁ ህዳሴ ግድብ ሲጠናቀቅ ሀይል አቅርቦቱን በ4 እጥፍ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ዋና ከተማው አዲስ አበባ በአየር ከአለም ጋር እየተገናኘች ሲሆን በዘመናዊ የባቡር መንገድ ግንባታም ሲስተም ጥሩ እድገት እያሳየች ነው፡፡



በትምህርትም ላይ መንግስት ጥሩ ኢንቨስት አድርጓል፡፡ እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ከ20% በታች የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2014 ወደ 94 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ እ.ኤ.አ በ1990 አንድ ዩኒቨርሲቲ የነበረ ሲሆን አሁን ከ30 በላይ ደርሰዋል፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ አሁን በቀላል ኢንዱስትሪ ላይ ብታተኩርም አላማው ግን ለበለጠ የኢንዱስትሪ መሰረት መጣል ነው፡፡

የመንግስት ንብረት የሆነው ሜቴክ ቀላል ተሽከርካሪዎች እና የአውቶሞቢል ኤንጂን እያመረተ ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2025 ለማሳካት የምትሻው ራዕይ **በኢሮስፔስ** መሪ መሆን ነው፡፡ ከአሁኑ  የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከደቡብ አፍሪካ በሽርክና የቦይንግ ኤር ባስ ክፍሎችን ለማምረት ተስማምታለች፡፡




ከቻይና ያላት ግንኙነት ከአሁኑ ፍሬ በማፍራት ላይ ነው፡፡ ከቻይና ቤልት እና የመንገድ ኢኒሼቲቭ ጋር በመተሳሰር በኢትዮጵያ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እ.ኤ.አ በ2016/17 4.2 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል፡፡

ኢትዮጵያ ፖሊሲዎቿ በግሎባላይዜሽን በጥብቅ መተሳሰርን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ሀገሪቱ ግሎባላይዜሽን / ሏላዊነት ስርዓት እንጂ አማራጭ አይደለም ብላ በማመን ከአለም ጋር በጥብቅ ለመተሳሰር አጥብቃ እተንቀሳቀሰች ነው፡፡ ከዚህም ተጠቃሚ እሆነች ነው፡፡ የኢትዮጵያ እድገት ልማት፣ ሰላም እና ዲሞክራሲ ግንባታ ከግሎባላይዜሽን ውጪ የሚታሰብ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያም ለኒውስ ዊክ በአንድ ወቅት እንደገለጸችው ለእድገቱ ለግሎባላይዜሽን እውቅና ሰጥታለች፡፡ የቻይና እድገት ለኢትዮጵያ አስተዋጽዖ እያደረገ ነው፡፡ በአሁኑ ሰአት በቻይና የጉልበት ዋጋ እየተወደደ በመምጣቱ ጉልበት ተኮር ኢንዱስትሪዎች ወደ ኢትዮጵያ እየተሰደዱ ነው፡፡ ፍሬደሪክ ኩ እንደሚለው ከሆነ 85 ሚሊዮን የስራ እድል የሚፈጥሩ ጉልበት ተኮር ኢንዱስትሪዎች ከቻይና ወደ አፍሪካ ይፈልሳሉ፡፡ በመሰረተ ልማት ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ እያፈሰሰች ያለችው እና የ100 ሚሊዮን ህዝብ ባለጸጋ ሆነችው ኢትዮጵያ ዋነኛው የቻይና ኢንዱስትሪዎች መዳረሻ ትሆናለች፡፡

## በታሪክ ሀብታሟ ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ አኩሪ ታሪክ ያላት አገር ነች፡፡ የባህል ማንነቷ በጣም ትልቅ ነው፡፡ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች በተለየ መልኩ ኢትዮጵያ ማንነት የተመሰረተው በቅኝ ገዢዎች ሳይሆን በኦርጋኒክ/ ተፈጥሮ የተገነባ ነው ያላል ፍሬደሪክ፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ ቀጠናው የሰው ልጅ የስልጣኔ መሰረት ነው፡፡ ከአርሜኒያ ጎን ለጎን ቀደምት የሀይማኖት አገር ናት፡፡ ያለምንም ጥርጥር በምደር ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ በአለም ላይ ካሉ በጣም የጥንት እና የበለጸገ ልምድ ነው፡፡ የአለም ስልጣኔ እና ጥንታዊ ገዳማትን ላሊበላ፣ ጎንደር ወዘተ. የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያውያኖች ኮሚዩኒኬት የሚያደርጉበት የራሳቸው የግእዝ ቋንቋ አላቸው፡፡



ፍሬደሪክ ጠንካራ ማህበረሰብ የሚመሰረተው በጠንካራ ባህል ላይ ነው ይላል፡፡ የሚያኮራ ታሪክ ያላቸው ሀገሮች ለራሳቸው ማንነት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ያለፈ ስኬታቸው እና በራስ መተማመን ላይ ስለሚያተኩሩ ነው፡፡



በባህል ሀብት፣ በታሪክ ኩራት እና ተለየ ማንነት ኢትዮጵያ አሁንም እንዳስጠበቀች ነው፡፡ የፍሬደሪክ የኢትዮጵያን ስልጣኔ እንደገና ለማደስ መሰራት ያለበት የቤት ስራዎች አሉ፡፡ እሱም ሳሙኤል ሀንቲንግተን እንደሚለው ከቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በኋላ የአለም ግጭት የሚያተኩረው በርዕዮተ አለም ሳይሆን በስልጣኔ ላይ ይሆናል የሚል ነው፡፡ ሀንቲንግተን እንደሚለው ከሆነ የምዕራቡ ስልጣኔ በአለም ላይ ካሉ 7 ስልጣኔዎች ማለትም የቻይና፣ የጃፓን፣ የአረብ፣ የሩስያ ኦርቶዶክስ፣ የአፍሪካ ቀንድ ስልጣኔዎች ጋር ግጭት ውስጥ ይገባል፡፡ እነዚህ ስልጣኔዎች በአግባቡ ካልተያዙ ወደ ከፍተኛ ብጥብጥና ግጭት ይቀየራሉ፡፡ ምክንያቱም የስልጣኔ ግጭቶች በዋነኝነት ከማንነት ጋር የተያያዙ ስለሆነ ነው፡፡

የአፍሪካ ቀንድ ካለው ጂኦፖለቲካዊ ጠቀሜታ አኳያ የባለብዙ ዋልታዎች የፍልሚያ ሜዳ ሆኗል፡፡ ጅቡቲን እንኳ ብንወስድ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ሪሲያ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች ወዘተ. እየተርመሰመሱበት እና እየተፋለሙበት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሀገሮች ጋር ኮሚዩኒኬት ስታደርግ የየአገሮቹን ኢኮኖሚ ሁኔታ፣

የፖለቲካ ምህዳር፣ ባህል ሚዲያና አክቲቪስቶች ሁኔታዎችን መተንተን እና በዚሁ ላይ የተመሰረተ መልዕክቶችን ቀርፆ ማስተላለፍ ይገባል፡፡ ለእያንዳንዱ አገር መልዕክት ስናስተላልፍ ከላይ የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች በመተነተን መሆን እንዳለበት የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ በአለም ላይ ልምድ እና ሰፊ መረብ ያላቸው የአለም አቀፍ ህዝብ ግንኙነት ኤጀንሲዎች መጠቀም ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ እነዚህ ተቋማት አለመኖር ከአለም የህዝብ ግንኙነት የተገለልን መሆናችንን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ኬንያ እንኳ አላት፡፡ ለዚህም ነው እኛ ቀውስ ውስጥ ስንገባ ቶሎ መውጣት የሚያቅተን፡፡ ቻይና ለኦሎምፒክ ስትዘጋጅ እነዚህን ተቋማት ተጠቅማለች፡፡ ከታይዋን ባለት ውዝግብ እነዚህን ተቋማት ተጠቅማለች፡፡ ከአሜሪካ ጋር ባላት ግንኙነት የአለም አቀፍ ኔት ወርክ ያላቸው የምዕራብውያንን የህዝብ ግንኙነት ተቋማት ተጠቅማለች፡፡

እኛም ኢኮኖሚውን የበለጠ ነጻ እያደረገ በመሆኑ ከኤርትራ ጋር ባለን ግንኙነት እና የወደብ አጠቃቀም ለህዳሴው ግድብ በተመለከተ እና ከአንዱ አገር ጋር የምናደርገው ግንኙነት ሌላውን ለመጉዳት አለመሆኑን በማስረዳት አለም አቀፍ የህዝብ ግንኙነት ተቋማት የማማከር ልምድ ብንጠቀም ጥሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ዘመኑ "Think global act local" የሚለው መፈክር ለጥሩና ቀጣይነት ያለው ግንኙነት እንደ መርህ ተቀባይነት ያገኘበት ዘመን ስለሆነ ነው፡፡




**ፀሀፊው ከአ/አ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነት እና ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን የማስተርስ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በ1986ከአ/አ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡**

**ዋቢ፤** Ethiopia becoming an industrial powerhouse and future "Wakaranda".FREDERICK KUO ASIA TIMES AUGUST 6, 2018